የሴቶች ማረፊያና ልማት ማህበር

በዚህ እትም:


- ሴማልማ የ16 ቀን ንቅናቄውን አከበረ
- በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የሴቶች ማረፊያዎች ህብረት ተቋቋመ
- ሴማልማ ከዝዋይ ከተማ ነዋሪዎች ጋር የአቅም ግንባታ እንቅስቃሴ አደረገ
- ለሴት ልጆች ምቹ የሆኑ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሴት ልጆች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን ይከላከላሉ
- ለሴቶች መብት ከቡርትካንማ ቀን የዘለለ ትኩረት


# ስሙኝ

## ሲማልማ የ16 ቀን ዘመቻውን አከበረ

‘16 የንቅናቄ ቀናት’ ወይም በኢትዮጵያ ነጭ ሪቫን ቀን ተብሎ የሚታወቀው የተባበሩት መንግስታት በሴቶች እና በህፃናት ላይ የሚደርሰውን ጥቃት ለማስቆም የሚያካሂደው አመታዊ ዘመቻ ነው፡፡ ከህዳር 25 እስከ ታህሳስ 10 ብርቱካንማ ቀለምን በመጠቀም ከጥቃት የተረፉ ሴቶችን ለማስታወስ እና በጉዳዩ ላይ ትኩረት እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡ በዚህ ወቅት የአፍሪካ ህብረት፣ የአሚሪካ ኤምባሲ ጽ/ቤት እና የአፍሪካ የኢኮኖሚ ኮሚሽንን የመሳሰሉ በአዲስ አበባ የሚገኙ ጎልተው የሚታዩ ቦታዎች በሴቶች ላይ የሚደርሰውን ጥቃት መከላከሉ ላይ የሚደረገውን እንቅስቃሴ በመደገፍ በቡርትካናማ ቀለም ያሸበርቃሉ፡፡ ‘በሴቶች ላይ የሚደርሰውን ጥቃት ለማስቆም ገንዘብ ማሰባሰብ’ የዚህ አመት ዋንኛ አጀንዳ ሲሆን ይኸውም የፆታ እኩልነትን ማስፈን በጉዳዩ ላይ ከሚፈሰው መዋለ ንዋይ  የበለጠ ጥቅም እንዳለው ለማሳየት ነው፡፡

ሴማልማ የ16 ቀናቱን ንቅናቄ በአዲስ አበባ እና በአዳማ ከተማ የተደረጉ እንቅስቃሴዎችን በመደገፍ እና በአዲስ አበባ ማረፊያዎች ከጥቃት ከተረፉ ሴቶች ጋር ሻማ የማብራት ስነስርዓት በማድረግ የዘመቻው ተሳታፊ ሆኗል፡፡ ሴማልማ በየካ ክፍለ ከተማ የሴቶች እና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ ተዘጋጅቶ 1500 ሰዎችን ያሳተፈውን የማህበረሰብ እና የባለ ድርሻ አካላት ስብሰባን በገንዘብ ደግፏል እንዲሁም በአዳማ የነጭ ሪቫን ቀን ለማክበር የተዘጋጀ ዝግጅት ላይ ድጋፍ አድርጓል፡፡




## በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የሴቶች ማረፊያዎች ህብረት ተቋቋመ

ኢትዮጵያ የመጀመሪያውን ከጥቃት የተረፉ ሴቶች ማረፊያዎች ህብረት (Ethiopian Network of Women Shelters) ጥቅምት 25 ቀን 2009 ዓ.ም. አቋቋመች፡፡ ህብረቱ በህዳር 2009 ዓ.ም ለማረፊያዎቹ UN Women ባዘጋጀው ስልጠና መጠናቀቂያ ላይ ነው የተመሰረተው፡፡ በስልጠናው ላይ በኢትዮጵያ የማረፊያ አግልግሎት ከሚሰጡ 13 መስሪያ ቤቶች የተውጣጡ 29 ተወካዮች ተሳትፈዋል፡፡ በአገሪቱ ካሉት መጠለያዎች በኦሮሚያ ክልል በአዳማ ከተማ የሚገኘውን ትልቁን መጠለያ የሚያስተዳድረው ሴማልማ የህብረቱ አስተባባሪ እና የጎዳና ተዳዳሪ ሴቶች መልሶ ማቋቋም ድርጅት (OPRIFS) ምክትል አስተባባሪ እንዲሆን ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡ ህብረቱ ዓመታዊ የተግባር ዕቅድ እና በመጀመሪያው ዓመት ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ሶስት ስራዎችን ማለትም ደረጃቸውን የጠበቀ ለሚመለከተው የማስተላለፍ (referral) ስርዓት ፣ጥምር የገንዘብ ማሰባሰብ ስራ እና ለውጦችን የማነሳሳት እንቅስቃሴዎችን ጨምሮ የሚሰራባቸውን አቅጣጫዎች ለይቷል፡፡


የሴማልማ ሰራተኞች በስልጠናው ላይ

ለሴቶች መልሶ ማቋቋም እና ለማህበረሰብ የማብቃት ተቋማቶች የተሰጠው የሶስት ቀን ስልጠና በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የተካሄደ ነው፡፡ ከምስራቅ ቲሞር በመጣች ባለሙያ የተመራው ስልጠና በUN Women እና በሌሎች ተባባሪ አካላት በ2015 (እ. ኤ. አ) በተዘጋጀው አለም አቀፍ የአገልግሎቶች መመሪያ ላይ ትኩረት አድርጓል፡፡ የሴቶች ማረፊያና ልማት ማህበር (ሴማልማ) በዚህ የአገልግሎትቶች መመሪያ ዝግጅት ላይ መሳተፉ ይታወሳል፡፡

*(ገፅ 2 ላይ ይቀጥላል)*

(ከገፅ 1 የቀጠለ)

በስልጠናው ላይ የተዳሰሱ ርዕሶች የሚከተለውን ያካትታሉ፡ የአፈፃፀም ሂደት፣ የምክር አገልግሎት፣ የመጠለያዎች መመሪያ ደንቦች፣ የህግ ድጋፍ አገልግሎት ለደንበኞች ፣ ለማህበረሰብ ማብቃት፣ የሰው እና የገንዘብ ሀብትን ማሰባሰብ፣ ማህበረሰቦችን የመድረስ እና ወደሚመለከተው የመምራት ስራዎች። የስልጠናው ተሳታፊዎች ልምዳቸውን በጥልቀት ተከፋፍለዋል፤ ከምስራቅ ቲሞር የመጣቸው አሰልጣኝም ልምዷን አካፍላለች።

የገንዘብ እና የማስፈፀም አቅም ውስንነት እና ሌሎች ምክንያቶች አንዳንድ ክፍተቶች ቢፈጥሩም በኢትዮጵያ ብዙዎቹ መጠለያዎች የአገልግሎት መመሪያውን ዋንኛ መርሆዎች እንደሚተገብሩ በስልጠናው ታይቷል። ደንበኞች ወደ ቤተሰቦቻቸው ለመመለስ ፍቃደኛ አለመሆን፣ በራሳቸው ህይወትን ለመጀመር አለመድፈር፣ በገንዘብ ራሳቸውን የመቻል ሙከራዎች አለመሳካት እና ሴቶች ስራ በሚውሉበት ጊዜ ልጆቻቸውን የሚያስቀምጡባቸው መዋያዎች ውድ መሆናቸው መጠለያዎቹ እንደ ዋንኛ ችግር የሚጠቅሱት ለማህበረሰብ የማብቃት ስራን አስቸጋሪ ከሚያደርጉት ምክንያቶች ውስጥ የተወሰኑት ናቸው። ሌላው በተሳታፊዎች የተጠቀሰው ችግር ከጥቃት ለተረፉት ሴቶች እና ህፃናቶች ምቹ ያልሆኑ የፍርድ ሂደቶች መንጓተት ነው። የህግ ብያኔ በጊዜው አለማግኘት ማለት ደንበኞቹ ከሚፈልጉት በላይ በማረፊያዎቹ እንዲቆዩ ይገደዳሉ ማለት ነው።

## ሴማልማ ለዝዋይ ከተማ ነዋሪዎች የአቅም ግንባታ ስራዎችን ሰራ

በሴቶች እና ህፃናት ላይ የሚደርሰውን ጥቃት ለመከላከል በኦሮሚያ ክልል የሚገኘው ሴማልማ ለዝዋይ ከተማ ነዋሪዎች ሶስተኛ ዙር የአቅም ግንባታ ስራዎችን ሰርቷል። ህዳር 24 እና 25 ቀን ዕድሜያቸው ከ13-15 ለሚሆኑ ታዳጊዎች የሁለት ቀን የክህሎት ማሳደጊያ ስልጠና ተሰጥቷል። እንዲሁም የማህበረሰብ ምክክር ከወላጆች እና መምህራን ከተውጣጣ ኮሚቴ እና ከማህበረሰብ አባላት ጋር ተደርጓል።.



የማህበረሰብ አባላት በምክክር ወቅት

በክህሎት ማሳደግያ ስልጠናው ላይ ተማሪዎች እራሳቸውን እና ሌሎችን ከጥቃት መከላከል እንዲችሉ ስለ ፆታ እና ስለ ፆታን ተገን አድርገው ስለሚደርሱ ጥቃቶች መሰረታዊ ትምህርት የተሰጣቸው ሲሆን በተጓዳኝም ስለ ጓደኛ ተፅዕኖ፣ በእርግጠኛነት መግባባት (assertiveness) እና የመሪነት ክህሎቶች ስልጠና አግኝተዋል። የሴማልማ ተወካዮች እና ፖሊሶች የማህበረሰብ ምክክሮቹን አስተባብረዋል። ምክክሩ የማህበረሰብ አባላት ልምዳቸውን ማካፈል እንዲችሉ እና ችግሩ ሲያጋጥማቸው ምን ማድረግ እንዳለባቸው ስምምነት ላይ እንዲደርሱ በማገዙ የማህበረሰብ አባላት በሴቶች እና ህፃናት ላይ የሚደርሰውን ጥቃት የመከላከል ስራ እንዲሰሩ አግዟቸዋል። ሴማልማ እነዚህን ስራዎች መስራቱ ድርጅቱ የጥቃት ተጠቂ ከሆኑ ሴቶች ጋር ባለው ጥልቅ ልምድ ምክንያት የጥረቱን አግባብነት የበለጠ ያጎላዋል።

በኦሮሚያ ክልል የሚገኘው ሴማልማ ከተመሰረተበት ከግንቦት 2007ዓ.ም. ጀምሮ እንደዚህ አይነት የክህሎት ስልጠናዎችን ለአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች በሰጠው ስልጠና 232 ተማሪዎች ተሳትፈዋል። እንዲሁም ከ400 በለይ ከሚሆኑ የማህበረሰብ አባላት ጋር የማህበረሰብ ምክክሮችን አድርጓል። በሴማልማ የተደረገ ጥናት በህገወጥ መንገድ ወደተለያዩ ከተሞች የሚዘዋወሩ ሴቶች እና ህፃናት የሚያርፉበት ቦታ በመሆኑ ምክንያት የሴቶች ጥቃት በስፋት የሚስተዋልበት ከተማ መሆኑን በማሳየቱ የዝዋይ ከተማ ለአቅም ግንባታ ስራው ሊመረጥ ችሏል።

## ለሴት ልጆች ምቹ የሆኑ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሴት ልጆች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን ይከላከላሉ

ገኖ ጂሎ በዝዋይ ከተማ የሴማልማ አቅም ግንባታ መርሃ ግብር ተጠቃሚ ከሆኑ ትምህርት ቤቶች ውስጥ አንዱ በሆነው በባቱ ቁጥር 2 አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ የእንግሊዘኛ ትምህርት መምህር እና የሴቶች ክበብ አስተባባሪ ናት። ገኖ በሴቶች ላይ ስለ ሚደርሰው ጥቃት የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ ለማስተማር ከቤተሰብ እና ከአስተማሪዎች የተውጣጡ ኮሚቴዎች ምክክር ላይ ትሳተፋለች። ገኖ እንዲህ ስትል ትናገራለች "ከዚህ የምክክር ስልጠና ብዙ ስለ ስለተማርኩ ሴት ተማሪዎቼ ምክር ፈልገው እኔ ጋር ሲመጡ እንዴት ማማከር እና መደገፍ እንዳለብኝ አውቄያለው።"

እውነትም ገኖ በሚገባ ተማሪዎቿን ትደግፋለች። የሴቶች ክበብ አባል የሆነችው የስምንተኛ ክፍል ተማሪዋ አማኒ የሚከተለውን ታሪክ አካፍላለች። "በትምህርት ቤታችን ወንድሟ ሊድራት የሚፈልግ አንዲት ልጅ ነበረች።" "ሊደርስባት የነበረውን ነገር ስትፈራ ስትቸር ለኛ አካፈለችን። እኛም የሴቶች ክበባችንን ለምትመራው አስተማሪያችን ለገኖ ስለጉዳዩ እንድትነግራት አሳመንናት። አስተማሪዋ ስለ ጉዳዩ እንደሰማች ያለ ምንም ማመንታት የልጅቷን ቤተሰቦች ለማናገር ሄደች። ልጅቷ ትምህርቷን እንድትቀጥል ሊረዷት እንደሚገባ እና ልጅቷን የመዳር ዕቅዳቸውን ካልተው ግን ለሚመለከተው አካል ለማመልከት እንደምትገደድ ገለፀችላቸው" ስትል አማኒ አብራርታ ገልፃለች።

በባቱ ቁጥር 2 አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ካሉት 2053 ተማሪዎች ውስጥ 1195ቱ ሴቶች ናቸው፤ ሴማልማ ከትምህርት ቤቱ ተማሪዎች ጋርም ይሰራል። ከ13- 15 ዓመት ለሆኑ ታዳጊዎች በፆታ፣ ፆታን ተገን ያደረጉ ጥቃቶች፣ የጓደኛ ተፅዕኖ እና በራስ የመተማመን ክህሎት ላይ ስልጠና ይሰጣል። የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር በሪሶ ነገሶ "በትምህርት ቤቱ በሴቶች ላይ ስለሚደርሱ ጥቃቶች ሰፊ የሆነ የማሳወቅ ስራ ተሰርቷል" ብለዋል። "አንድ ተማሪ ተደፍራ የሶስት ወር ነፍሰ ጡር ስለሆነች በጣም እንደተከፋች እና እራሷን ማጥፋት እንደምትፈልግ አንዲት ተማሪ ነገረችን እኛም ጉዳዩን በሚገባ መረመርነው። ጉዳዩን ለፖሊሶች አሳውቀን ልጅቷን ወደ ሴማልማ ላክናት።"

ሴት ልጆች ከትምህርት ቤት ሲቀሩ አስተማሪዎች እና ርዕሰ መምህራን ለጉዳዩ የሚገባውን ትኩረት ሰጥተው ቤተሰቦቻቸውን የልጆች ጋብቻን የመሳሰሉ ጉዳዮች ላይ ያነጋግራሉ። በትምህርት ቤቱ ጊቢ ውስጥ የሴት ተማሪዎች የራሳቸው መፀዳጃ ቤት ስለ ተሰራላቸው ትምህርት ቤቱ ደህንነት እና ድጋፍ የሚያገኙበት ቦታ እንደሆነ ይሰማቸዋል። የሴማልማ ጣልቃ መግባት ለፆታ ጉዳይ ትኩረት የሚሰጥ፣ በሴቶች እና በህፃናት ላይ የሚደርስ ጥቃት በዝምታ የማይታይበት ለሴቶች ምቹ የሆነ ማህበረሰብ እንዲፈጠር አግዟል።



በሪሶ ነገሶ እና ገኖ ጅሎ

**"በትምህርት ቤቱ በሴቶች ላይ ስለሚደርሱ ጥቃቶች ሰፊ የሆነ የማሳወቅ ስራ ተሰርቷል።"**

የዚህን መፅሄት ቅጂ በኢሜይል ለማግኘት info@awsad.org ላይ መልዕክት ይላኩ

የሴቶች ማረፊያና ልማት ማህበር (ሴማልማ) ዋንኛ ለጋሾቹን ማመስገን ይፈልጋል:

- **NPA**
- **UNFPA (ኔዘርላንድስ ኤምባሲ)**
- **UN Women (አይሪሽ ኤይድ እና የዳኒሽ ቆንስላ በኢትዮጵያ)**
- **ውማን ካይንድ ወርልድ ዋይድ**
- **ኮሚክ ሪሊፍ**
- **ኢትዮጵያኤድ (ዩኬ፣አይርላንድ፣ አውስትራሊያ)**

የሴቶች ማረፊያና ልማት ማህበር (ሴማልማ) በኢትዮጲያ የሚገኝ በጎ አድራጎት ማህበር ሲሆን የተቋቋመውም የሴቶችን ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን የላቀ ለማድረግ እና አካላዊ እና ስነ ልቦናዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ሴቶች እና ታዳጊ ሴት ልጆች ድጋፍ ለመስጠት ነው። ሴማልማ በአዲስ አበባ እና በኦሮሚያ ክልል አዳማ ከተማ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል።

በማረፊያ ቤቱ ሴማልማ ምግብ፣ስነልቦናዊ ድጋፍ፣ ጊዜያዊ መጠለያ፣ የህክምና አገልግሎት እና መሰረታዊ ትምህርት እና ክህሎቶችን የሚያዳብሩ ስልጠናዎችን ለተጠቃሚዎች ይሰጣል። ከ1996 ዓ.ም. ጀምሮ ሴማልማ ከአራት ሺህ በላይ ለሚሆኑ ሴቶች እና ህፃናት አገልግሎቱን ሰጥቷል። (**በዚህ ሩብ ዓመት ብቻ ሴማልማ ለ279 ሴቶችና 162 ልጆቻቸው አገልግሎቱን ሰጥቷል።**) ለመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች፣ ፖሊስ ፣ የሴቶች እና የህፃናት ጉዳይ ቢሮ እና ለሌሎች ባለድርሻ አካላት የአቅም ግንባታ ስልጠናም ይሰጣል።

የሴቶች ማረፊያና ልማት ማህበር

ስልክ: +251 116672290

ፋክስ: +251 116625461

ኢሜይል: awsad950@gmail.com



## ለሴቶች መብት ከቡርትካንማ ቀናቶቹ የዘለለ ትኩረት

በማሪያ ሙኒር፣ የሴማልማ ዋና ዳይሬክተር

16 የንቅናቄ ቀናት (ወይም የነጭ ሪቫን ቀን በመባል የሚታወቀው) የሚከበርበት የህዳር ወር በሴቶች ላይ የሚደርሰውን ጥቃት ማስቆም ላይ ለምንሰራ ሰዎች የምንደሰትበት ወቅት ነው። ከህዳር 16 – ታህሳስ 1 የተባበሩት መንግስታት 16 የንቅናቄ ቀናትን በሴቶች ላይ የሚደርሰውን ጥቃት ለማስቆም ዓለም ዓቀፍ 'የቡርትካን ቀለም' ዘመቻን ያከብራል። ይህ ወቅት ጉዳያችን በመገናኛ ብዙሃን፣ በባለድርሻ አካላት እንዲሁም በህዝቡ ውስጥ የተለየ ተደማጭነት የሚያገኝበት እና ከሴቶች ጥቃት ነፃ የሆነች ዓለምን ስለ መፍጠር ደግመን ደጋግመን ድምፃችንን ለማሰማት ዕድል የምናገኝበት ወቅት ነው። እኔ ግን በሴቶች ላይ የሚደርሰውን ጥቃት የማስቆም ጉዳይ አሳሳቢ ሊሆን የሚገባው እና ዓመቱን ሙሉ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ አለመሆኑ ይደንቀኛል። ችግሩ እርግጥም በጣም ስር የሰደደ ነው። ተንሰራፍቷል በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃት በዓለም ዓቀፍ ደረጃ የተስፋፋና ከጠቅላላው ህዝብ ግማሽ የሚሆነው ህዝባችን ላይ ተፅዕኖ ያመጣ ዋንኛ የሰው ልጆች የመብት ጥሰት ነው። በየቀኑ ሴቶች እና ህፃናት ሥነ ልቦናዊ፣ አካላዊ እና ወሲባዊ ጥቃቶች ይደርስባቸዋል፤ በተጨማሪም ዕድገታቸውን የሚገድቡ ፆታዊ የሆኑ ችግሮችን ይጋፈጣሉ። ከስነ ምጣኔ አንፃር ይህ ምርታማ መሆን የሚችሉ ሴቶች በመቀነሳቸው፣ ለህክምና እና ለፍትህ ሲባል ከሚወጣው ወጪ በተጨማሪም በሚቀንሰው ወይም በሚጠፋው ገቢ ምክንያት ለግለሰቦችም ሆነ አጠቃላይ ለስነ ምጣኔውም ከፍተኛ ወጪ ነው። ከምንም በላይ ግን ከሞራል አንፃር ሲታይ በማህበረሰብ ደረጃ የትክክለኛ ባህርይ አለመላበስ እና ቅንነት አለመኖር እና ከባድ ኢ- ፍትሃዊነት ነው። በሴማልማ በየቀኑ አስደንጋጭ የሆኑ የሴቶች ጥቃት ምሳሌዎች ስለሚያጋጥመን ጉዳዩ ሁሌም በዓዕምሯችን ቀዳሚ ቦታን ይይዛል። ስለዚህ ሴቶች እና ህፃናት ላይ የሚደርሰው ጥቃት ሁልጊዜ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። እያንዳንዱ የአመቱ ቀናት ከቤታችን፣ ከማህበረሰባችን እና ከዓለማችን የሴቶችን ጥቃት ለማጥፋት የምንሰራባቸው የንቅናቄ ቀናት መሆን አለባቸው።